# ኦርቶዶክሳዊ ሥነ ጽሑፍ

## የኦርቶዶክሳዊ ሥነ ጽሐፍ ይዘት

መንፈሳዊ /ኦርቶዶክሳዊ/ ሥነ ጽሑፍ ዓላማው ነገረ እግዚአብሔርን ማስተማር ምግባረ ሃይማኖትን መስበክ ነው። የሥነ ጽሑፉ ግብ፤ እግዚአብሔር ለሰዎች ያደረገውን ቸርነት፣ የሰውንና የእግዚአብሔርን ግንኙነት፣ የቅዱሳንን ገድል፣ የጠላት ዲያብሎስን ግብር ወዘተ በማሳየት ሰውን በእምነቱ ጸንቶ እንዲኖር መምከር ነው።

ይህን የሥነ ጽሐፍ ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሲጻፍ የሚከተሉትን ነገሮች ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል።

1.እውነታንና የገሐዱን ዓለም ሕይወት የሚያመለክት መሆን
2.የቤተ ክርስቲያንን እምነት፣ ሥርዓትና ትውፊት መጠበቅ
3.በይዘቱ በቋንቋው በስልቱ የተደራሲያንን ዕድሜ፣ እውቀት፣ ባህልና አኗኗር ያገናዘበ መሆን
4.ኦርቶዶክሳዊ ለዛ /ላህይ/ አገላለጽ ያለው መሆን አለበት
ምሳሌ:- እመቤታችንን፡ እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ፣
ጊዮርጊስን፡ ሊቀ ሰማዕታት ቅዱስ ጊዮርጊስ
ሙሴን ሊቀ ነቢያት ሙሴ እያለ ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምባቸውን ቃላት መጠቀም ይገባል።

5. ለሥነ ጽሑፉ መነሻ የሚሆኑ ነጥቦችን ቤተ ክርስቲያን ከምትቀበላቸው ቅዱሳት መጻሕፍትና ሊቃውንተ ቤተ ክርስተያን ትምህርት መውሰድ

6. አጠራጣሪ ታሪኮች ካልሆኑ በስተቀር በዶግማና በቀኖና ጉዳይ ላይ ሳይሆን አይቀርም፣ ተብሎ ይታመናል፣ ይነገራል የሚል አገላለጽ መጠቀም ተገቢ አይደለም።

### በኦርቶዶክሳዊ ሥነ ጽሐፍ ዘርፍ ሊዳሰሱና ግንዛቤ ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸው ነገሮች

#### 1. ነገረ መለኮት

ነገረ መለኮት ሲነሣ የትምህርት ምንጭ የሚሆኑት
ሀ. ቅዱሳት መጻሕፍት
ለ. ሊቃውንት አባቶች ተርጉመው ያስተማሩት ትምህርት
ሐ. ቤተ ክርስቲያንን የምትጠቀምባቸውን አባባሎች መጠቀምመ. ነው ወይም አይደለም የሚል መደምደሚያ ያለው መሆን

#### 2. ነገረ ቤተ ክርስቲያን

ነገረ ቤተ ክርስቲያን ሲነሣ የትምህርት ምንጭ የሚሆኑት
ሀ. ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ማወቅ
ለ. የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ማወቅ
ሐ. የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት መጠንቀቅና መጠበቅ ያስፈልጋል።

ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሲነሣ ማን ጀመረው? የት? ለማን? እንዴት ይፈጸማል? ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ ሊሆን ይገባዋል።

3. ስብከት

ስብከት መረጃ መስጠትን ሳይሆን ማሳመንንና መለወጥን ይመለከታል። የምእመናንን ችግር ለመፍታት ለማጽናናትና ለመምከር እንዲሁም ሕይወታቸውን ለመለወጥ ለማጽናት የሚደረግ ስለሆነ በቅዱሳት መጻሕፍት መመሪያነት አኗኗራችንን ማኅበራዊ ሕይወታችንን ከቅዱሳን ሕይወት ጋር እያመሳከርን ማስተማር መቻል አለብን። ስብከቱ ምእመናን የሚጠይቁአቸውን ጥያቄዎች ሊመልስ እና ችግርም ካለ የሚፈታ ሊሆን ይገባል።

4. የቅዱሳት መጻሕፍት ጥናት

የቅዱሳት መጻሕፍት ጥናት ሲባል እንደ ሌሎች የጥናት ዘርፎች በምርምር እውነት ነው ወይስ አይደለም ወደሚል መደምደሚያ የሚመራ አይደለም። የግል አስተያየት /መላምት/ አይሰጥም። በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተው ቅዱሳን ሰዎች የጻፉአቸውን መጻሕፍት ለመረዳት፣ ለምን እንደ ተጻፉ ለማወቅ፣ ለምን እንደሚጠቅሙ ለመለየት፣ እንዴት እንደሚነበቡ ወዘተ የሚያስረዳ ሥነ ጽሑፍ መሆን አለበት።

5. የቅዱሳን ሰዎች ታሪክና የቅዱሳን መካናት ታሪክ

የቅዱሳን ሰዎችን የተጋድሎ ታሪክ መሠረት አድርጌ ምእምናንን ለማስተማር ይቻላል። እንዲሁም ምእመኑ የቅዱሳን መካናት ታሪክ እንዲረዳ በረከት እንዲያገኝ እንዲንከባከባቸው የሚያስረዳ ሥነ ጽሑፍ ይጻፋል።

6. ማኅበራዊ ጉዳዮች

ምእመናን በሚኖሩበት ማኅበረሰብ በሚኖራቸው ማኅበራዊ መስተጋብርና ሚና የሚገጥሟቸውን ችግሮች /ጉዳዮች/ የሚዳስስ ነው።

## ሀ. ኦርቶዶክሳዊ ሥነ ግጥም

ኦርቶዶክሳዊ ሥነ ግጥም በሥነ ጽሑፍ ታሪክ ቀዳሚ እንደሆነ ይነገራል። የሰው ልጅ ፊደል ቀርጾ ጽሑፍ ከመጀመሩ በፊት በግጥም አምላኩን ሲያመሰግንበት ሀዘን እና ደስታውን ሲገልጽበት ኖሯል። በቤተ ክርስቲያን ታሪክም በትክክል በዚህ ዘመን ተጀመረ ለማለት ቢያስቸግርም እጅግ ጥንታዊ ስለመሆኑ ግን አሌ አይባልም። ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝሙረ ዳዊት፣ መጽሐፈ ኢዮብ፣ ከአዋልድ መጻሕፍት መልክዓ መልክዕ እና ሰላምታ እንዲሁም የቅዱስ ያሬድ ድርሰት ድጓ ግጥማዊ ናቸው። መዝሙር ስብሐተ እግዚአብሔር ማድረሻ ነው፡ እስራኤል ከግብጽ ባርነት ነፃ ወጥተው ባሕረ ኤርትራን ሲሻገሩ በክብር ከፍ ከፍ ብሏልና ብለው አመስግነዋል። ዘጸ.15ሚ21።

## ለ. የመንፈሳዊ ግጥም ምንነትና ባሕርያት

መንፈሳዊ ግጥም ስለአንድ ጭብጥ ነገር አድምቆና አጉልቶ የማሳየት ችሎታ ያለው በጥቂት ምርጥ ቃላት ሰፊ መልእክትን ማስተላለፍ የሚችል ነው። ትኩረቱ በክርስቲያኖች ሕይወት ዙሪያ ነው። ጸሐፊው ስሜቱን የሚዳስሰውን ሐሳብ፣ ትዕይንት በራሱ ፈጠራ አዋቅሮ አቀናጅቶ የሕይወትን ሥዕል አስውቦ ያቀርባል። ግጥም የተለያየ ይዘት ቅርጽና ግብ ስለሚታይበት አንድ ወጥ ብያኔ ለመስጠት ከባድና አስቸጋሪ ነው። ከዚህ ይልቅ መለያ ባሕርያቱን መቃኘቱ የተሻለ ነው።

## 1. ምትና ምጣኔ

ምት የቀለማት፣ የቃላት፣ የሐረጋትና የስንኞች ምጣኔ ነው። ምጣኔ ሲዛባ ምት ይጠፋል። ግጥሙም ዜማ አይኖረውም። ግጥም ዜማውን ጠብቆ እንዲጓዝ አንድ ሐረግ ሲነበብ የሚወስደው ጊዜ ከሚቀጥለው ሐረግ ጋር እኩል ሆኖ ለእዝነ ህሊና መደመጥ አለበት።
የምጣኔ ዓይነቶች
በግጥም አጻጻፍ በስፋት የሚያገለግሉ ሦስት ዓይነት ምጣኔዎች አሉ።

ሀ. የወል ቤት ግጥም ምጣኔ

በስንኝ 12 በሐረግ 6 ቀለማት ያሉት ግጥም ነው።
ለምሳሌ፡ጠ ለታረደው በግ ለመድኃኔዓለም 12
ምስጋና ይድረሰው እስከ ዘለዓለም 12

ለ. ሰንጎ መገን ቤት ምጣኔ

ሰንጎ መገን ቤት ምጣኔ በስንኝ 10 በሐረግ 5 ቀለማት ይኖሩታል።
ምሳሌ፡- አቤቱ አንተን እጣራለሁ 10
ነፍሴን ወደ አንተ አነሣለሁ 10

ሐ. የቡሄ በሉ ቤት ምጣኔ

በስንኝ 8 በሐረግ አራት ቀለማት ይይዛል።
ምሳሌ፡- የዚያን ለታ ጐልጐታ 48
የዓለም ጌታ ሲንገላታ 48
ሦስቱንም ስልቶች አደባልቆ መጻፍም የተለመደ ነው። እነዚህን አደባልቆ መጻፍም ብልህነት ነው።

## 2. የቃላት ምርጫ

ግጥም እምቅነትና ቁጥብነት ሊኖረው ይገባል። ሰፊ ሐሳብን በጥቂት ቃላት ለመግለጽ የቃላት ምርጫው ብርቱ ጥንቃቄን ይፈልጋል። በእርግጥ የመንፈሳዊ ግጥም ተቀዳሚ ዓላማ ውል ያለው መልእክት ማድረስ ነው። መልእክቱ ከልብ ዘልቆ ሰውን ለንስሐ እንዲዘጋጅ ሰማያዊውን ነገር እንዲያስብ ከበደል እንዲርቅ የእግዚአብሔርን ቸርነት እንዲገነዘብ ለምስጋና እንዲተጋ የሚቀሰቅስ ሊሆን ይገባዋል። ምሳሌዎችንና ዘይቤዎችን መጠቀም ግጥሙን ያደምቀዋል።

## 3. ይዘት

መንፈሳዊ ግጥም የግጥምን ባሕርያት አሟልቶ ለውበት ብቻ የሚጻፍ አይሆንም። አጽንኦት የሚሰጠው ለመልእክቱ ነው፣ ጸሐፊው በመረጠው ርእስ ዙሪያ ነጥቦችን አንሥቶ ሲያወጋ የሚከተሉትን ነጥቦች ልብ ሊል ግድ ነው።

# ሀ. እምነት

ከቤተ ክርስቲያን እምነት ውጪ የሆነ ሐሳብ በግል አስተሳሰብ፣ ግምትና ፍልስፍና

በመጻፍ አንባቢን ወደአልተፈለገ መስመር መውሰድ አይገባም::
ምሳሌ:- ይለመንሻል ለአንቺ ለእናቱ
እኔንስ እምቢ አለ ጸናበት አንጀቱ
እየቆምኩኝ ጧት ማታ ከቤቱ::

ይህ ግጥም ከቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ውጪ ነው:: ምክንያቱም እግዚአብሔር በባሕርይው መሐሪና ይቅር ባይ እንጂ ልመናችንን የማይሰማ ጨካኝ አምላክ አይደለም:: እኛ ግን በበኩላችን ከፊቱ ልንቆም አይገባም በማለት እመቤታችንን አንቺ ንጽሕት ነሽና ለምኝልን እንላለን::

## ለ. ሥርዓት

የግጥሙ መልእክት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን የሚያፋልስ መሆን የለበትም:: ገጣሚው የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ጠንቅቆ ማወቅና በአግባቡ መግለጽ አለበት::

ምሳሌ:- በአምላክ አደባባይ ከቤተ መቅደሱ
ካህናት ሲቆሙ ስሙን ሊቀድሱ
ላስቀድስ ሄድኩና እኔም እንደነርሱ
የጀመርኩት መጽሐፍ ልክ አሐዱ ሲባል
ባነብ አላልቅ አለኝ እትው እሰኪባል::

በቤተ ክርስቲያን የቅዳሴ ሥርዓት ቅዳሴ እየተቀደሰ ቅዳሴ አቋርጦ መጽሐፍ ዘርግቶ የግል ጸሎት ማድረስ ሥርዓት አይደለም:: ስለዚህ ግጥሙ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት የጠበቀ አይደለም::

## ሐ. ትውፊት

በግጥም የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት መጠበቅ ተገቢ ነው:: የቅዱሳት ሥዕላትን አሣሣል የሕንፃ ቤተ ክርስቲያንን አሠራር፣ አለባበስ፣ የንዋያተ ቅዱሳትን አጠቃቀም ማዛባት ተገቢ አይደለም::

ምሳሌ:- ጸናጽል መቋሚያ ከበሮውን ይዘው
ማኅሌት ሲቆሙ ቅድስት ውስጥ ሆነው
መንፈስን ያድሳል ከልብ ላስተዋለው::

ግጥሙ የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት የጠበቀ አይደለም:: ምክንያቱም ካህናት ማኅሌተ እግዚአብሔር የሚቆሙት ቅኔ ማኅሌት ውስጥ እንጂ ቅድስት ውስጥ አይደለም::

## መ. ጥቅል ሐሳብ

ግጥም አንድ ነገርን በመዘርዘር ከመናገር ይልቅ ሰብሰብ አድርጌ በሳል መልእክትን ያስተላልፋል:: ገጣሚም ይህንን ልብ ሊል ይገባል::
/ይቆየን/

ወስብሐት ለእግዚአብሔር